# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
# አዕማደ ምስጢራት
# (Ethiopian Orthodox Tewahido Church Pillars of Mysteries)

1. ምስጢረ ሥላሴ (Mystery of Trinity)
2. ምስጢረ ሥጋዌ (Mystery of Incarnation)
3. ምስጢረ ጥምቀት (Mystery of Baptism)
4. ምስጢረ ቁርባን (Mystery of Holy Eucharist)
5. ምስጢረ ትንሣኤ ሙታን (Mystery of Resurrection of dead)

# አምስቱ አዕማደ ምስጢራት፥ መግቢያ

## The Five Pillars of Mysteries: Introduction

# ይዘት
# (Outline)

- ❖የአንዳንድ ቃላት ትርጉም (Definition of terms)
- ❖አዕማድ ማለት ምን ማለት ነው? (The meaning of ‘Pillar’)
- ❖ለምን ምስጢራት ተባሉ? (Why do we call them ‘Mysteries?’)
- ❖አዕማደ ምስጢራት ምን ምን ናቸው? (What are the five Pillars of Mysteries?)
- ❖የአዕማደ ምስጢራት መሠረት ምንድን ነው? (The basis for Pillars of Mysteries)
- ❖አዕማደ ምስጢርን ማወቅ ለምን ይጠቅማል? (Why should we know them?)

# የአንዳንድ ቃላት ትርጉም
# (Definition of some Terms)

**እግዚአብሔር:**

“እግዚእ” ማለት ጌታ ማለት ነው፡፡

“ብሔር” ማለት ደግሞ ዓለም ማለት ነው፡፡

እግዚአብሔር ማለት የዓለም ጌታ (ፈጣሪ፣ ገዥ) ማለት ነው፡፡ ዘፍ 1፡1

**God:**

Pantocrater - The creator and ruler of the universe (Gen 1:1)

Lover of Mankind; Heavenly Father

Source of all moral authority

The supreme being; Almighty

# እምነትና ሃይማኖት
# (Faith and Religion)

**እምነት:**

- ማመን ወይም መታመን ማለት ነው፡፡
- ማመን የሰሙትንና የተረዱትን እውነት ነው ብሎ መቀበል ነው፡፡ ሮሜ 10፡17
- መታመን ያመኑትንና የተቀበሉትን እምነት በሰው ፊት መመስከር (በተግባር መግለጥ) ነው፡፡ ማቴ 10፡32 ያዕ. 2፡14-26
- ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ፥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው። ዕብ 11፡1

**Faith:**

- Firm conviction
- Faithfulness –Believe in heart and confess in mouth (manifest in deeds) Romans 10:9
- The substance of things hoped for, the evidence of things not seen. Hebrew 11:1

# እምነትና ሃይማኖት
# (Faith and Religion)

## ሃይማኖት:

- ለዓለም ፈጣሪ አለው ብለው የሚያምኑት እምነት ነው።
- ለዓለም ፈጣሪ አለው ብለው የሚመሰክሩት ቃል ነው።
- ሰው ፈጣሪውን የሚያመልክበት፣ ከፈጣሪው ጋር የሚገናኝበት፣ የእግዚአብሔር ልጅ የሚሆንበት፣ ጽድቅንም የሚሠራበት፣ የዘላለም ሕይወትን የሚያገኝበት መንገድ ነው።

## Religion:

- Believing in God (Organized Faith)
- Relationship with God
- Worshipping God
- The true way to eternal life

# ዶግማና ቀኖና
# (Dogma and Canon)

**ዶግማ:**

- የእምነት መሠረት ማለት ነው፡፡
- አይጨመርበትም፤ አይቀነስበትም፤ አይሻሻልም፡፡
- ችግርና ፈተናም ቢመጣ እስከ ሞት ድረስ አጥብቀን የምንይዘው ነው፡፡

**Dogma:**

- Basic principles at the heart of faith
- Professed as essential by all the faithful
- Incontrovertible

# ዶግማና ቀኖና
# (Dogma and Canon)

**ቀኖና:**

- ሥርዓት ማለት ነው፡፡
- በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው ያደጉ ክርስቲያኖች የሚመሩበት ሥርዓት ነው፡፡ (1ኛ ቆሮ. 14፥40)
- በቅዱስ ሲኖዶስ አማካኝነት እንደጊዜው ሁኔታ የሚሻሻል ነው፡፡

**Canon:**

- Ecclesiastical (church) law/rule (1 Corr 14:40)
- ‘Governs’ the church
- Formulated by Holy Synod
- Can be amended by Holy Synod

# ቤተክርስቲያን
# (Ecclesia)

የክርስቲያኖች ኅብረት/አንድነት (1ኛ ቆሮ 11፡28)

የክርስቲያኖች መኖሪያ፡ የእግዚአብሔር ቤት (ዮሐ 2፡16)

የእያንዳንዱ የክርስቲያን ሰውነት (1ኛ ቆሮ 3፡16)

Ecclesia - Congregation (1 corr 11:28)

Church - The place of worship (John 2:16)

God’s Temple - Individual Christians (1 Corr 3:16)



# አዕማድ ማለት ምን ማለት ነው?
# (What do we mean by “Pillar?”)

**አዕማድ:**

- አምድ ምሰሶ ማለት ነው፡፡
- አዕማድ ምሰሶዎች ማለት ይሆናል፡፡
- ምሰሶ ቤትን ደግፎ እና አቅንቶ ይይዛል፡፡
- አዕማደ ምስጢራት ሃይማኖትን አቅንተውና ደግፈው ይይዛሉ፡፡

**Pillar:**

- A vertical structure that support a building
- An important idea, principle or belief
- Pillars of mystery – anchors of faith



# ለምን ምስጢራት ተባሉ?
# (Why do we call them 'Mysteries?')

- ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊና ሃይማኖታዊ ትምህርት በመሆናቸው (1ኛ ቆሮ 2፡7-8)
- በሥጋዊ ጥበብና ምርምር መረዳት ስለማይቻሉ (1ኛ ቆሮ 2፡9)
- ላመኑት እንጂ ላላመኑት ሰዎች የተሰወሩ በመሆናቸው (ማቴ. 7፡6፣ ማቴ. 13፡11)

- These are religious beliefs based on divine revelation (1 Cor. 2:7-8)
- Difficult or impossible to understand or explain (1 Cor. 2:9)
- Can not be fully and exhaustively conceptualized or understood
- Are for those who believe in God

# አዕማደ ምስጢራት ምን ምን ናቸው?
# (What are the Five Pillars of Mysteries?)

- ምሥጢረ ሥላሴ (የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት) – Mystery of Holy Trinity
- ምሥጢረ ሥጋዌ (የአምላክን ሰው መሆን) – Mystery of Incarnation
- ምሥጢረ ጥምቀት (ስለ ዳግም መወለድ) – Mystery of Baptism
- ምሥጢረ ቁርባን (ስለ ክርስቶስ ሥጋና ደም) – Mystery of Holy Eucharist
- ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን (ስለ ዳግም ምጽዓት) – Mystery of Resurrection of the dead

# የአዕማደ ምስጢራት መሠረት ምንድን ነው?
# (What's the basis for Pillars of Mysteries?)




የጌታና የሐዋርያት ትምህርት

ጸሎተ ሃይማኖት - ጉባዔ ኒቂያ፣ ኤፌሶንና ቁስጥንጥንያ

ብሉያትና ሐዲሳት

Teachings of Jesus and his disciples

Creed of Faith – Nicea, Ephesus, Constantinople (Oriental Church)

Bible - Old and New Testament

# ጸሎተ ሃይማኖት

ሁሉን የፈጠረ አንድ አምላክ በሚሆን **በእግዚአብሔር አብ** እናምናለን።

ሰማይና ምድርን የፈጠረ የሚታየውንና የማይታየውን ዓለም ሳይፈጠር ከርሱ ጋር በነበረ አንድ የአብ ልጅ በሚሆን **በአንድ ጌታ በኢየሱስ** ክርስቶስ እናምናለን ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ እውነተኛ አምላክ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ በባሕርዩ ከአብ ጋር የሚስተካከል ሁሉ በእርሱ የሆነ በሰማይም ካለው በምድርም ካለው ያለርሱ ምንም ምን የሆነ የለም።

ስለኛ ስለሰዎች እኛን ለማዳን ከሰማይ ወረደ በመንፈስ ቅዱስ ግብር ከቅድስት ድንግል ማርያም **ፍጹም ሰው ሆነ**፤ደግሞ ስለኛ ተሰቀለ በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን እርሱ መከራን ተቀበለ ሞተ ተቀበረ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ፤ በቅዱሳን መጻህፍት እንደተጻፈ በክብር በምስጋና ወደሰማይ ዐረገ። በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ፤ ዳግመኛም በሕያዋንና በሙታን ለመፍረድ በምስጋና ይመጣል ለመንግስቱም ፍጻሜ የለውም።

**በመንፈስ ቅዱስም** እናምናለን እርሱም ጌታ ሕይወትን የሚሰጥ ከአብ የሠረፀ ከአብ ከወልድ ጋራ በአንድነት እንሰግድለታለን እናመሰግነዋለን እንርሱም በነቢያት አድሮ የተናገረ ነው።

ከሁሉም በላይ በምትሆን ሐዋርያት በሠሯት በአንዲት ክብርት **ቤተክርስቲያን** እናምናለን። ኃጢአት በሚሠረይባት በአንዲት **ጥምቀትም** እናምናለን **የሙታንንም መነሣት** ተስፋ እናደርጋለን የሚመጣውንም ሕይወት ለዘላለሙ።

# The Creed of Faith

We believe in one God, **God the Father** the Pantocrator who created heaven and earth, and all things seen and unseen.

We believe in one **Lord Jesus Christ**, the Only-Begotten Son of God, begotten of the Father before all ages; Light of Light, true God of true God, begotten not created, of one essence with the Father, by whom all things were made; Who for us men and for our salvation came down from heaven, and was **incarnate** of the Holy spirit and the Virgin Mary and became Man. And He was crucified for us under Pontius Pilate, suffered and was buried. And on the third day He rose from the dead, according to the scriptures, ascended to the heavens; He sits at the right hand of his Father, and He is coming again in His glory to judge the living and the dead, Whose kingdom shall have no end.

Yes, we believe in the **Holy Spirit**, the Lord, the Life-Giver, Who proceeds from the Father, Who with the Father and the Son is worshipped and glorified, who spoke by the prophets. And in one holy, catholic and apostolic **church**. We confess one **baptism** for the remission of sins. We look for the **resurrection** of the dead, and the life of the coming age. Amen.

# አዕማደ ምስጢርን ማወቅ ለምን ይጠቅማል?
# (Why should we Know the Pillars of Mysteries)

- ሃይማኖትን በሚገባ ለመረዳት
- ከጥርጥርና ከኑፋቄ ለመጠበቅ
- በሃይማኖት ጸንቶ ጽድቅን ለመፈጸም

- To better understand our faith
- To be protected from heresies
- To attain righteousness
- To get eternal life



# አጠቃላይ የምስጢራቱ አቀራረብ
# Approach to Pillars of Mysteries

1) ትርጉምና አስፈላጊነት (Meaning and importance)
2) የምስጢሩ ዋና ዋና ይዘቶች (Key aspects of the mystery)
3) የመጽሐፍ ቅዱስ አስረጅዎች (Evidence from scripture)
4) የሚያብራሩ ምሳሌዎች (Analogies)
5) በብዛት የሚነሱ ኑፋቄዎች (Common heresies)
6) ጥያቄዎች (Questions)